
# Find It፣ Fix It
# የማህበረሰብ ፕሮጀክት የገንዘብ ሽልማቶች
## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## Find It፣ Fix It የማህበረሰብ የእግር ጉዞዎች የሚባሉት ምንድናቸው?

ከ 2014 ጀምሮ፣ የ Seattle መኖሪያ ሠፈሮችን በአንድ ጊዜ አንድ ብሎክ በማሻሻል ለመርዳት የሚያስችል የ Find It፣ Fix It የማህበረሰብ የእግር ጉዞዎች፣ ከንቲባ Ed Murray እየመሩ ቆይቷል። በነዚህ የእግር ጉዞዎች ወቅት፣ የማህበረሰቡ አባሎች፣ ስለ መኖሪያ ሠፈር አስፈላጊ ነገሮች ከከንቲባ Murray ጋርና ከሌሎች የከተማው ባለሥልጣኖች ጋራ በቀጥታ የመናገር ዕድል ያገኛሉ። ከማህበረሰብ የእግር ጉዞዎች በኋላ፣ ከተማውና ማህበረሰቡ፣ በእግር ጉዞው ወቅት የተነሱትን ችግሮችን ለመፍታት አብረው ይሰራሉ።

**የ 2016 Find It፣ Fix It መኖሪያ ሠፈሮች፥**

- Aurora Licton Urban Village - ማክሰኞ፣ ግንቦት 31
- Belltown – በሰኔ መጨረሻ አካባቢ
- Roxhill / Westwood – ሐምሌ
- Judkins Park – ነሐሴ
- Georgetown – መስከረም
- Crown Hill / Whittier Heights – ጥቅምት
- Wallingford – ኅዳር




*በ 2015 ውስጥ፣ የ Hillman City የማህበረሰብ አባሎች ከ Find It፣ Fix It የማህበረሰብ ፕሮጀክት የገንዘብ ሽልማት በተገኘ ገንዘብ ተጠቅመው በአንድ ተመላላሽ በሚበዛበት የሕዝብ መተላለፊያ ላይ የሚገኙ አያሌ የአበባ ሳጥኖችን አሻሽለው አዘጋጅተዋል።*

## Find It፣ Fix It የማህበረሰብ ፕሮጀክት የገንዘብ ሽልማት ሲባል ምንድን ነው?

በ 2016 ውስጥ የ Find It፣ Fix It የመኖሪያ ሠፈር የማህበረሰብ አባል ከሆኑ፣ የመኖሪያ ሠፈርዎን ደህንነት ወይም መልክ ለማሻሻል የሚያስችል ፕሮጀክትን ለማጠናቀቅ እስከ $5000.00 ድረስ ለማግኘት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።

## ለማህበረሰብ ፕሮጀክት የገንዘብ ሽልማት ማመልከቻ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

የሽልማት ማመልከቻዎችን ከኢንተርኔት በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይችላሉ www.seattle.gov/finditfixit። በሠፈርዎ ውስጥ የ Find It፣ Fix It የማህበረሰብ የእግር ጉዞ ከሚካሄድበት ጊዜ አንድ ሳምንት በፊትና አንድ ሳምንት በኋላ ለእያንዳንዱ ሠፈር ማመልከቻ ማስገቢያ ጊዜ ክፍት ይሆናል። ወደ ቤትዎ በወረቀት ኮፒ እንዲላክልዎት ከፈለጉ፣ **Laura Jenkinsን በ** laura.jenkins@seattle.gov **ወይም 206.233.5166** ያነጋግሩ።
ማመልከቻዎች በእንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ፣ ሶማልኛ፣ ካንቶኒዝ፣ ቬትናምኛ፣ አማርኛና ታጋሎግ ተጽፈው ይቀርባሉ።

## ለ Find It፣ Fix It የማህበረሰብ ፕሮጀክት እንዴት መክፈል እችላለሁ?

የ City of Seattle ለፕሮጀክትዎ አስቀድሞ ገንዘብ ሊሰጥዎ አይችልም። ይህም፣ ፕሮጀክትዎን በግልዎ ወይም የመጀመሪያዎቹን ወጪዎች በመክፈል ሊረዱዎ ከሚችሉ ድርጅቶች ጋራ በመተባበር መክፈል ያስፈልግዎታል ማለት ነው። ለፕሮጀክትዎ የሚሆን ሁሉን ነገር ከገዙ በኋላ፣ የ City of Seattle በ 2 ሳምንቶች ውስጥ ወጪዎን ይተካልዎታል። ለፕሮጀክትዎ አስቀድመው መክፈል የማይችሉ ከሆኑ፣ አይጨነቁ። ስለ ሌሎች አማራጮች ለማወቅ **Laura Jenkinsን በ** laura.jenkins@seattle.gov **ወይም 206.233.5166** ይጠይቁ።

## ለማህበረሰብ ፕሮጀክት የገንዘብ ሽልማት ማመልከቻ ካላስገባሁ፣ ወደ Find It፣ Fix It የማህበረሰብ የእግር ጉዞ መሄድ

አዎ! ለማህበረሰብ የእግር ጉዞ አብረዎት እንዲመጡ ጓደኞችዎን፣ ቤተሰቦዎንና ጎረቤቶችዎን እንዲጋብዙ እናበረታታዎታለን።

## ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም ደግሞ ተጨማሪ መረጃ ከፈለግሁ ማንን ማነጋገር እችላለሁ?

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ **Laura Jenkinsን በ 206.233.5166** ያነጋግሩ። ሲደውሉ የሚናገሩትን ቋንቋ ይግለጹና በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አስተርጓሚ በስልክ ይቀርብልዎታል።